## ይኸ ቀን ያንተ ነው 1

**በአቤ ኮስትሬ**

ቢያሥቅ ቢያፍለቀልቅ
በሃዘን ቢያሰቅቅ
ቢዘገይ ቢፈጥን ከነችሮታው
ይህ የሚቸረን ቀን የሁላችን ነው
ይኸ ቀን ያንተ ነው ሌሊቱን ጨምሮ
በደስታ ሊያሰክርህ በጭንቀት ወጥሮ !
ቀንህን አውቀኸው ተጠቀምበት
በፌዝ ባሉባልታ አትዋልበት

ሥራህ ላይ ልትቆይ ወይ ልትባረር
ሹመት ልትላበስ ወይም ልትሻር
ሰዎች ሊያሳዝኑህ ልታሳዝናቸው
ሥቀው ሊያጃጅሉህ በፌዝ በቧልታቸው
ጸሐይ ተፍለቅልቃ ልታሟሙቅህ
ዝናሙ አረስርሶ ብርዱ ሊጎዳህ
ከጤናማው አየር ደስ ከሚያሰኘው
አልፎ ሲያጋጥምህ የተመረዘው
ትኩሳት ጉንፋኑ እያስነጠሰህ
አላፊና አግዳሚው ይማርህ ሲሉህ
ሁሉን ልትቋደስ ቀን የሚቸርህን
አይቀሬ ነውና ዕወቅ ግዴታህን
ድግሥ ልትበላ
ድግሥህ ሊበላ
ሙሽሪትን ይዘህ ልትገባ ከጫጉላ
ከበሮህ ሊመታ
ከበሮ ልትመታ
በደስታ ልታዜም ልትረግጥ ዳንኪራ
ደፍረህ ልትጀግን ወይም ልትፈራ
ይኸ ቀን ያንተ ነው ሌሊቱን ጨምሮ
በደስታ ሊያሰክርህ በጭንቀት ወጥሮ !!

የነገን አታውቅም ነግ ለራሱ ያውቃል
ዛሬን ልታውቅበት ብልኅነት ይሻል !!
የዛሬው ቀን ቢሆን ለነገው መሠላል
ዛሬን ካላወቅኸው ነገ ምን ይጠቅማል ?
ዛሬ ነገን አልፈህ ሳምንታት ወራትን
ልታልፍ ዓመታትን ተስፋ ብትሠንቅም
ዛሬን ሳታውቅባት ነገን አታውቃትም
ነግደህ ልታተርፍ ሠርተህ ልትሾም
ገበሬ ልትሆን ዘርተህ ልትቅም !
ዓልመህ ልትመታ ልትሆን ወታደር
ወገን ልትጠብቅ ያገርህን ዳር ድንበር
ጸሐፊ ልትሆን ቢሮ ሠራተኛ
ልትሆን ብትሻ ፍትሕ ሰጪ ዳኛ
በሁሉም አቅጣጫ በሥምሪትህ
ምርጫህን ልትከውን ዛሬ ነው ቀንህ
በታላላቅ ሙያ በኪነ-ጥበባት
በቴያትርና  በድምፃዊ ውበት
በሙዚቃ ሥራ በጋዜጠኛነት
ሾፌርም ብትሆን ወይም ስፖርተኛ
ደራሲም ብትሆን የዕውቀት መገኛ
ይኸ ቀን ያንተ ነው ሌሊቱን ጨምሮ
በደስታ ሊያሰክርህ በጭንቀት ወጥሮ !!

በሰከንድ ደቂቃ በሂደተ-ሰዓት
የሰዎች ተግባራት በሚከወንባት
በዚህች ዓለማችን በምንኖርባት
ጊዜዋን ተጋርተን ስንማማርባት
እኔም አንተም እርሷ እንቋደሳለን
ከዓለሟ ስጦታ የት እናመልጣለን ?

ዓለም ብትፈካ ሲያሻት ብትጨልም
ሲያሻት አስደስታ ሲያሻት ብታስቆዝም
በችግር በሥቃይ በኀማም ብትገርፍም
በጌጥ አሽቆጥቁጣ ሀብትን ብታጠግብም
ዓለም ሳትናገር በዝምታ አታልፍም
ትናገረዋለች የራሷን ፍላጎት
ወሳኝ ነችና የሁሉም እመቤት
ሰላም ጦርነትን እያፈራረቀች
ደስታና ሃዘንን ለሁሉ እየቸረች
እንደ ስጦታዋ ሁሉ እያስተዋላት
አንዱ ሲያመሰግን ሌላው ሲያማርራት
መልሳ ስትወስድ የቸረችውን
ሰባብራ ስትጥል የጎበዘውን
ከላይ የነበረው ወርዶ ከታች አምባ
ሣቁ ተነጥቆበት በልቅሶ ሲያነባ
ከታች የነበረው ከማማው ላይ ወጥቶ
በደስታ ሲሰክር ሰቆቃውን ረስቶ
ዓለም ብትነፍገን ሲያሻት ብትቸረን
ጥላና አንስታ ብትወዘውዘን
ብታርገፈግፍፈን ብታመናጭቀን
ብሩሁን አዕምሮ አፍዝዛ ብታስቀር
ከዝምታ አልፈን ምንስ ልንናገር ?
ቀኑን አውቀንበት ልንጠቀምበት
ጠንክረን ልንሠራ በዕውቀት ልናድግበት
ብልኀነት ብቻ ይጠበቃል ከኛ !
ተስማምተን ለመኖር ሳንሆን ተንኮለኛ !!